# ADDA BILISUMMAA OROMOO

OROMO LIBERATION FRONT

جبهة تحرير أورومــو


Gaafa: 23-01-2012 تاريخ
Date:

Lakk.: 002/stm-abo/2012 رقم
No.:

***የኦሮሞ ህዝብ ኣብዮት ኣስተባባሪ ጉባኤና ብሄራዊ የወጣቶች ንቅናቄ ለነፃነትና ለዴሞክራሲ (ቄሮ) ያቀረቡት የኣብዮት ጥሪ በሰፊው የኦሮሞ ህዝብና በተቀሩት የሃገሪቷ ህዝቦች መደገፍ ይገባዋል***

የኦሮሞ ህዝብ ኣብዮት ኣስተባባሪ ጉባኤና ብሄራዊ የወጣቶች ንቅናቄ ለነፃነትና ለዴሞክራሲ (ቄሮ) እነሆ ታሪካዊ ጥሪ ኣቅርበዋል። ጥሪያቸውም ሰላማዊ የኣብዮት ጥሪ ነው። ከኦሮሞ ህብረተሰብ በወጡት በ ነዚህ ስብስቦች መሪነት የሚጠራው ሰላማዊ ኣብዮት ኣላማው ኣጭርና ግልፅ ነው- የመለስ ዜናዊን የ ጭቆና ስርኣት ማስወገድ። ይህ በሁለቱ ንቅናቄዎች የተደረገው የጋራ ጥሪ ላለፉት ኣስር ኣመታት ሳይቋረጥ በኦሮምያ የተካሄደው የረ ጭቆና ኣመፅ (FDG) ቀጣይ ኣካል ነው።

ይህ ታሪካዊ ጥሪ የቀረበው በኦሮምያና በሌሎችም የሃገሪቷ ክልሎች ኣጅግ ወሳኝ በሆነ ጊዜ ነው። በሁሉም የህብረተሰቡ ክፍሎች በተለይም በኦሮሞ ተወላጆች ላይ የሚካሄደው የጅምላ እስራትና ግድያ ወደር የማይገኝለት ደረጃ ላይ በደረሰበት ጊዜ ነው። በተለይም በኦሮምያ የኦሮሞው ኣባወራ ጎጆ እን ዲፈርስ ተደርጎ ከሩቅ ቦታ በመጡ ባለሃብቶች ቪላና ፎቅ የሚታነፅበት ወቅት ነው። ባለመሬቱ ዜጋ በቀዬው ላይ የሚገባውን ክብር ተነፍጎ ቀዬውን ለወረሰው መጤ ባለሃብት ኣጎብድዶ በዋርዲያነትና በገረድነት እንዲያገለግል የተፈረደበት ጊዜ ነው። ከዚህም በተጨማሪ ወቅቱ የኑሮ ውድነት የማይቀመስ ደረጃ ላይ በመድረሱ የህይወት ተስፋ የጨለመበት ዘመን ነው። የተፈጥሮ ኣካባቢ እንዲበከልና እን ዲወድም እየተደረገ ያለበት ኣደገኛ ወቅት ነው። ባጠቃላይ ሰዉ ብቻ ሳይሆን የሃገሪቷ ምድርም በተለይም ኦሮምያ በየቀኑ የሚፈምባትን ግፍና በደል መሸከም ኣቅቷት ሉሉሉ እያለች የድረሱልኝ ጣር የሚታሰማበት ወቅት ነው ቢባል ማጋነን ኣይሆንም።

እንዲህ ባለው ኣስከፊ ጊዜ ከህዝብ ኣብራክ ወጥተው በተደራጁ ወገኖች የሚቀርበው የኣብዮት ጥሪ ፍትሃዊ ነው። የወቅቱ ጥያቄ የወለደው ክቡር ኣላማ ያነገበ ጥሪ ነው። ስለሆነም የሁሉም የህብረተሰቡ ክፍሎች ተሳትፎ ሊደረግለት የሚገባው ነው። በኣረቡ ኣለም የተነሳውና ኣንዳንድ ኣምባገነን መንግስ ታትን ኣስወግዶ ሌሎችንም ነቅሎ ለመጣል የተቀጣጠለው *ዘ ኣረብ ስፕሪንግ* የሚል መጠሪያ የተሰጠው ኣብዮትም የህዝብ ኣብዮት ነው። ኦሮሞና እንደሱ ሁሉ የጭቆናው ገፈት ቀማሽ የሆኑ የሃግሪቷ ህዝቦች ሁሉ ተባብረው የኣረቡን ኣለም ኣይነት ስኬታማ ኣብዮት የማያካሄዱበት ምንም ምክንያት ኣይኖርም። በተለይም የኦሮሞ ህዝብ በኢትዮጵያ ተቀጣጥሎ የመለስ ዜናዊን ኣምባገነናዊ ኣገዛዝ ማስወገድ የ ሚገባውን ኣብዮት የመጀመሪያ ችቦ መለኮስና ኣብዮቱንም መርቶ ከግቡ ማድረስ የብዙሃንነቱ ሚና ይሆናል።

የኦሮሞ ነፃነት ግንባር የኦሮሞ ህዝብ የነፃነት ትግል መሪ ድርጅት እንደ መሆኑ መጠን ይህንን የኦሮሞ ህዝብ ኣብዮታዊ ንቅናቄ በሙሉ ልብ ይደግፋል፣ ለስኬታማነቱም የሚጠበቅበትን ኣስተዋፅኦ ያበረክታል። ለኦሮሞ ህዝብ ነፃነት የሚታገል ድርጅት በመሆኑ ህዝቡ ተደራጅቶ ነፃነቱን ለማረጋገጥ በሚንቀሳቀስበት ወቅት ይህንን ኣንቅስቃሴ ለመደገፍና ለማበረታታት የመሪ ድርጅታዊ ሃላፊነት የተጣለበት እሱው ላይ ነው። ይህን ስንል ግን፣ ይህ በሰላማዊ መንገድ የሚካሄደው ኣብዮት የህዝብ ኣብዮት (nonviolent people’s revolt) እንደመሆኑ መጠን ኦነግ እንደ ድርጅት ከሚከተከው የትግል ስትራቴጂ ጋር ተቆራኝቶ መታየት የለበትም። የተጀመረው ኣብዮት የህዝቡ ኣንገዛም ባይነት ኣመፃ (civil disobedience) ስለሆነ ሃገር ኣስ ተዳድራለሁ የሚለው መንግስት ለዚህ የህዝቡ ሰላማዊ ጥያቄ ተገቢውን ሰላማዊ ምላሽ የመስጠት ሃላፊነት ኣለበት።

ሃገር ቤትና በውጪው ሃገራት የሚኖረው ህዝብ ልጆቹ ያቀጣጠሉትን ይህንን ኣብዮት በኣካልና በመን ፈስ ተረባርቦ ከግቡ እንዲያደርሰው ኦነግ ጥሪውን ያቀርባል። በተለይም የኦሮሞ ህዝብ ሰሜን ደቡብ፣


P. O. Box 6973 Asmara, Eritrea | Telefax 291 1 153848 | E-mail abamilki@gemel.com.er

ምስራቅ ምእራብ ሳይል በሁሉም የዞኖቹ ከተሞች የኣብዮት ኣደባባዮችን ኣበጅቶ በመሰባሰብ የ
ኣንገዛም ባይነት ድምጹን ከፍ ኣድርጎ እንዲያሰማ ታሪክ ጥሪ ኣድርጋለታለች። ወንድ ሴት፣
ትልቅ ትንሽ ሳይል ተማሪው፣ ኣስተማሪው፣ ነጋዴው፣ ኣርሶ ኣደሩ፣ መንግስት ሰራተኛው፣
ሃብታሙ፣ ድሃው፣ ባጠቃላይ ሁሉም የህብረተሰቡ ክፍሎች (from all walks of life) በኣብዮቱ
ውስጥ መሳተፍ ኣስፈላጊ ይሆናል። በሃገር ቤትና በውጪው ኣለም የሚገኙ ሁሉም የፖለቲካ
ድርጅቶች (ኦፒዲኦም ጭምር) ከዚህ የኦሮሞ ህዝብ ኣብዮት ጎን እንዲቆሙ ጥሪ እናስ
ተላልፋለን።

እንዲህ ያለው ኣብዮት ከፍተኛ የኣላማ ፅናትና ትእግስት እንደሚጠይቅም መዘንጋት የለበትም።
ይህ በሰላማዊ መንገድ የሚካሄደው ኣብዮት ቀናት፣ ሳምንታት፣ ወራት ወይም ኣመታት ሊወስ
ድ እንደሚችል ኣስቀድሞ በመረዳት ሙሉ ፅናትና ትእግስትን በመሰነቅ መዘጋጀት ያስ
ፈልጋል። በትግሉ ጎዳና ላይ ሊያጋጥሙ የሚችሉትን ማናቸውንም እንቅፋቶችን በድል
መወጣት ይቻል ዘንድ የግብፅ ህዝብ በካይሮ ታህርር ኣደባባይ ያስመዘገበውን ድል ማስታወስና
ኣስፈላጊ ልምዶችንም መቅሰም ጠቃሚ ይሆናል።

በዚሁ ኣጋጣሚ በሃገሪቷ መከላከያ፣ ፖሊስ፣ ፈጥኖ ደራሽ፣ ሚሊሻና ደህንነት ሃይሎች ውስጥ የ
ተሰለፋችሁ የህዝብ ልጆች በሙሉ! የኣምባገነኑን የወያኔ መንግስት ኣላማ ለማሳካት ሲባል ባዶ
እጁን ለመብቱ ለመታገል በሚወጣው ህዝባችሁ ላይ ከመተኮስና ድብደባ ከመፈም በእጅጉ እን
ድትቆጠቡ ኦነግ ወገናዊ ጥሪውን ያቀርብላችህዋል። በተለይም በነዚህ የመንግስት መለዮ ለባሽ
ሃይሎች ውስጥ የተሰለፋችሁ የኦሮሞ ተወላጆች ከነሙሉ ትጥቃችሁ ከህዝባችሁ ጎን በመሰለፍ
ኣብዮቱን የምታቀላጥፉበት ወቅት ኣሁን መሆኑን እናስታውሳችህዋለን። የሚካሄደው ኣብዮት የ
ህዝባችሁ ብቻ ሳይሆን የሙሉ ቤተሰባችሁ ኣባላት ኣብዮት ነው። ኣብዮቱ ያነገባቸው ጥ
ያቄዎችም የራሳችሁም ጥያቄዎች መሆናቸውን ኣስታውሱ።

ከኦሮሞ ህዝብ ጋር ተመሳሳይ የጭቆና እጣ የገጠማችሁ ብሄር ብሄረሰቦች ሆይ! በኦሮሞ ህዝብ
በተቀጣጠለው በዚህ ኣብዮት ውስጥ ተቀላቅላችሁ የጋራ ጠላታችሁ ለሆነው ኣምባገነኑ
የወያኔ ስርኣት ፍፃሜ ማበጀት ይጠበቅባችሁዋል። ኣብዮቱ ጨቋኞኙን ስርኣት ነቅሎ ለመጣል
ያለመ ኣንደመሆኑ መጠን የጭቆናው ሰለባ የሆኑት የሁሉም ህዝቦች ኣብዮት ነው። የጋራ
ጠላትን ለማስወገድ የተጀመረ ኣብዮት ነውና የሁሉም ወገን ተሳትፎ ይጠይቃል። በተለይም
እንደ ሸገር ባሉ ታላላቅ ከተሞች ከፍተኛ ኣብሮኣዊነትን በማንባረቅ ኣብዮቱ የውጭ መገናኛ
ብዙሃንን ትኩረት እንዲስብ በጋራ መስራት ኣስፈላጊ ይሆናል። በዴሞክራሲ ስም የሚነግደውን
ና ዘረፋ፣ እስራት፣ ግድያ፣ ኣፈናና ድብደባን ፖሊሲው ኣድርጎ ህዝብን የሚገዛውን ኣምባገ
ነን ስርኣት ኣስወግዶ በምትኩ ሰላም፣ ነፃነት፣ ዴሞክራሲና ብልፅግና እውን የሚሆኑበትን ስርኣ
ት ለመዘርጋት ሁሉም በዚህ ኣብዮት ላይ እንዲሳተፍ ጥሪ እናደርጋለን።

ኣለም ኣቀፉ ማህበረሰብና ለሰብኣዊ መብቶች መከበር የቆሙ ወገኖች ሁሉ ይህንን ኣብዮት የ
መደገፍ የሞራል ግዴታ ኣለባቸው። ኣብዮቱ ላለፉት መቶ ሰላሳ ኣመታት በህዝቦች ላይ የተጫ
ነውን ኣስቀያሚ የጭቆና ቀንበር ለመጣል የሚካሄድ ኣብዮት ኣንደመሆኑ መጠን እንደ ሌሎቹ
ሃገራት ኣብዮቶች ሁሉ ድጋፍ ይገባዋል።

**ድል ለኦሮሞ ህዝብ!**

**የኦሮሞ ነፃነት ግንባር**
**ጥር 23, 2013**